# የዘመኑ ጀግኖች

**ክፍል 2**

ፀሃዬ ደባልቀው

ዋሽንግተን ዲሲ

ኢትዮጵያ ሀገሬ መልከ ዥጉርጉር፤
የጥንቱ አርበኞች የዛሬም ጭምር፤
የሲማሊ ጀግና ዑመር ሰመተር፤
መሃመድ አብዲለሃሰን እውቁ ስመጥር፤
የድል ወምበራ ዝና የእንሰቷ ነብር፤
የሃረሪው ጀግና ይገባታል ክብር፡፡
የአፋር አርበኞች እስቲ ይታወሱ፤
ጦረኛው ሙዚንጌርን ወግተው የመለሱ፡፡
ታጋይ ቢል ቱክ ተኳሽ የጋምቤላው ልጅ፤
መትረየስ ትራሱ ተራማጅ በፈንጅ፡፡
የቤኒሻንጉል አውራ ዝናው የገነነ፡፡
ሽክ ኦጀሌ ሲባል ጠላቱ ባነነ፡፡
መች እነዚህ ብቻ ሃገሬ ኢትዮጵያ፤
አሉሽ መርጥ ልጆች ለስሞሽ መጠሪያ፡፡
የትላንቱ ገድል በዘመኑ ጥበብ፤
ታድሶ ጎልብቶ ጠንክሮ እንዲያብብ፡፡
ቃል ኪዳን ገቡልሽ መሃላ ፈፀሙ፤
ረሃብ ድንቁርና ጨርሶ እንዲያከትሙ፡፡
ድህነት ቡትቶ ውርዶት እነዲጠፋ፤
ልማት ብልጽግና ዕድገት እንዲስፋፋ፡፡

ሁሉም በሃገሩ ተማምኖ በህብረት፤
ማንነቱ ታውቆ ቋንቋ ተከብሮለት ፤
መልካም አስተዳደር ፍትህዊ አንድነት፤
ዲሞክራሲ ሰፍኖ የህዝብ ወሳኝነት፤
ሙሉእ በኩለሄ በተግባር በሂደት፤
እስኪረጋገጡ ያሏዳች ማመንታት፤
ሁሉም ዘብ ይቆማል ይሰራል በትጋት፤
አገሬም ትለምልም ትራመድ ወደፊት፤
በዘመኑ ጀግኖች በልጆቿ ኮርታ፤
ለዘለአለም ትኑር ኢትዮጵያችን ፀንታ።